የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ

የመንግስት የልማት ድርጅቶች ዲስክሎዠር አፈፃፀም መመሪያ

507/2013

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Public Enterprises Holding and Administration Agency

ጥር 2011 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

I. መግቢያ

የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ የልማት ድርጅቶችን በበላይነት የማስተባበርና የመምራት እንዲሁም የመቆጣጠር ኃላፊነት የተጣለበት በመሆኑ፤

የመንግስት የልማት ድርጅቶች ውጤታማ፣ ተወዳዳሪና አትራፊ እንዲሆኑ ዘመናዊ የኮርፖሬት አስተዳደርና ኮርፖሬት ፋይናንስ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የመንግስት የልማት ድርጅቶችን አሰራርን በመከታተል፣ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ግልጽነትና ተጠያቂነትን በተላበሰ መንገድ ለመተግበር የሚያስችል አንዱ መንገድ አለምአቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የዲስክሎዠር አፈጻጸም ስርዓት ወጥና ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የልማት ድርጅቶች አፈፃፀም ለሁሉም ባለድርሻ አካላት በታወቀ አሰራር መረጃቸውን ይፋ ማድረግ ተወዳዳሪነታቸውን እና ዓለምአቀፍ ተቋማት ጋር የሚያደርጉትን ግንኙነት የሚያጠናክርና እምነት የሚያስገኝ በመሆኑ፤

የመንግስት ልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ባወጣው ደንብ ቁጥር 445/2011 አንቀጽ (5) ንዑስ አንቀጽ (3) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን የዲስክሎዠር አፈጻጸም መመሪያ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የዲስክሎዠር አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር **507/2013**" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

2.1. **"ኤጀንሲ"** ማለት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ ነው፡፡

2.2. **"የመንግስት የልማት ድርጅት"** ማለት በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/84 አንቀጽ 2(1) የተመለከተውን ትርጓሜ የሚያሟላ ድርጅት ወይም አክሲዮኖቹ ሙሉ በሙሉ ባለቤትነት የተያዙ አክሲዮን ማህበር ሲሆን በሌሎች ሕጎች ወይም በመንግስት ውሳኔ የተለየ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን የተሰየመላቸውን ድርጅቶች አይጨምርም፡፡

2.3. **"ቦርድ"** ማለት በአዋጅ ቁጥር 25/84 አንቀጽ 10/2/ እና አንቀጽ 12 መሰረት የመንግስት የልማት ድርጅቶችን በበላይነት እንዲመራ፣ እንዲቆጣጠርና ውሳኔ እንዲሠጥ የሚሰየም የድርጅት የሥራ የአመራር ቦርድ ነው፡፡

2.4. **"ዋና ሥራ አስፈጻሚ"** ማለት አንድን የልማት ድርጅት ወይም አክሲዮን ማኅበር የሚመራ ዋና ኃላፊ ነው፡፡

2.5. **"ማኔጅመንት"** ማለት ዋና ሥራ አስፈፃሚ እና ተጠሪነታቸው ለዋና ሥራ አስፈፃሚ የሆኑ የልማት ድርጅቱ የሥራ አመራር አባላት ናቸው፡፡

2.6. **"ዲስክሎዠር"** ማለት የልማት ድርጅቱ ወቅታዊና ትክክለኛ የሆነ የፋይናንስ እና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የአፈጻጸም እና ለውሳኔ የሚረዱ መረጃዎችን ለባለድርሻ አካላት ይፋ ለማድረግ የሚያስችል ስርዓት ነው፡፡

2.7. **"ፋይናንስ ነክ መረጃዎች"**፡- ማለት በልማት ድርጅቱ የሚዘጋጁና ትክክለኛነታቸው የተረጋገጡ የሂሳብ መግለጫዎች/ Statement of financial position, Income

statement, statement of cash flow, statement of Owners equity/ እና አባሪ ማብራሪያዎችን የያዘየድርጅቱ የፋይናንስ መረጃዎች ናቸው፡፡

2.8. "ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ መረጃዎች"፡- ማለት የልማት ድርጅቱ የምርት እና ሽያጭ፣ የገቨርናንስ ፣የህግ ጉዳዮች፣ ማህበራዊ ግንኙነትና ኃላፊነት፣ ኢኮኖሚያዊ፣ አካባቢያዊጉዳዮችን ያካተቱ መረጃዎች ናቸው፡፡

2.9. "ባለድርሻ አካላት"፡- በልማት ድርጅቱ የሥራ እንቅስቃሴ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ድርሻ እና ህጋዊ ፍላጎት ያላቸው አካላት ሲሆኑ የድርጅቱን ሰራተኞች፣ አበዳሪዎች፣ አቅራቢዎች፣ ደንበኞች፣ ተቆጣጣሪ አካላት፣ የአስተዳደር አካላትና የማኀበረሰብ አካላትን ያጠቃልላል፡፡

2.10. በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ የሚጨምር ሆኖ በነጠላ የተገለፀው ለብዙም ያገለግላል፡፡

3. የመመሪያው የተፈፃሚነት ወሰን፡-

ይህ መመሪያ ለኤጀንሲው ተጠሪ የሆኑ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Public Enterprises Holding and Administration Agency

ክፍል- ሁለት

2. መመሪያው የሚመለከታቸው አካላት ኃላፊነት፤

2.1 የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ ተግባርና ኃላፊነት፣

2.1.1 ሁሉም የመንግስት የልማት ድርጅቶች በወጥነት የሚተገብሩት የዲስክሎዠር አፈፃፀም መመሪያ ያወጣል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

2.1.2 የልማት ድርጅቶች መረጃ በማደራጀት ወቅታዊ የሆነ የተጠቃለለ መረጃ (Aggregate Disclosure) ለባለድርሻ አካላት ይፋ የሚደረግበትን የአሠራር ስርዓት ያዘጋጃል፣ ተግባራዊ ይደርጋል፤

2.1.3 የልማት ድርጅቶች የተሟላ እና ወቅታዊ መረጃዎችን ለህዝቡና ለተለያዩ የሚመለከታቸው አካላት በየጊዜው ማሠራጨታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ የማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡

2.2 የሥራ አመራር ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት፣

2.2.1 በኤጀንሲው የተዘጋጀውን የልማት ድርጅቶች የዲስክሎዠር አፈጻጸም መመሪያ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡ በየጊዜው በአፈፃፀሙ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለይቶ የማስተካከያ ዕርምጃ ይወስዳል፤ በመመሪያው ላይ ሊሻሻሉ የሚገባቸው ጉዳዮች ሲያጋጥም የማሻሻያ ሀሳብ ለኤጀንሲው ያቀርባል፤

2.2.2 ማናቸውም የህዝብ ግንኙነት ሥራዎች በኃላፊነትና በተጠያቂነት እንደዚሁም በግልጽ በሚታወቅ ባለቤት ውጤታማ በሆነ መንገድ መካሄዳቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

2.2.3 በልማት ድርጅቱ ይፋ የሚደረጉ እና በሚስጢር የሚያዙ መረጃዎችን ባህሪና ምንነት በሚመለከት ግልጽ ፖሊሲ እንዲቀረጽ ያደርጋል፣ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

2.2.4 እንደ ቦርድ ስብሳቢው ወይም በወኪሉ አማካኝነት ድርጅቱን በሚመለከት መግለጫ ይሰጣል፤

2.2.5 የልማት ድርጅቱ የዲስክሎዠር አፈፃፀም በተመለከተ ለኤጀንሲው የተሟላ ሪፖርት ያቀርባል፤ በኤጀንሲው የሚጠየቁ መረጃዎችን በተሟላ ሁኔታ ያቀርባል፣ ወይም እንዲቀርብ ያደርጋል፤

2.2.6 የሥራ አመራር ቦርዱ ይህ የዲስክሎዠር አፈጻጸም መመሪያ በተሟላ ሁኔታ ሥራ ላይ እንዲውል ካላደረገ ወይም በዲስክሎዠር ስርዓቱ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ የተደረጉ የልማት ድርጅቱ መረጃዎች ትክክለኛ ካልሆኑ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

2.3 የልማት ድርጅቱ ሥራ አመራር (ማኔጅመንት) ተግባርና ኃላፊነት፤

2.3.1 የልማት ድርጅቶች የዲስክሎዠር አፈጻጸም መመሪያ በሚፈቅደው መሰረት የልማት ድርጅቱ መረጃዎች በአግባቡና ወቅቱን በጠበቀ ሁኔታ አዘጋጅቶ ለሥራ አመራር ቦርድ ያቀርባል፤ የሥራ አመራር ቦርዱ የቀረበለትን ሪፖርት የተሟላና ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ ዲስክሎዝ እንዲደረግ ሲወስን በተመረጡ ዘዴዎች መረጃዎቹን ዲስክሎዝ ያደርጋል፤

2.3.2 የኮርፖሬት ዲስክሎዠር የሚመራበትን አሠራር እና ተጠያቂነት በግልጽ የሚያመላክት የውስጥ አሰራር በማዘጋጀት በሥራ አመራር ቦርድ አስጸድቆ ተግባራዊ ያደርጋል፤

2.3.3 የኮርፖሬት ዲስክሎዠር አፈፃፀም መመሪያ በትክክል ስለመተግበሩ የሚከታተል አካል እንዲሠየም ያደርጋል፤ አመራር ይሠጣል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ሪፖርት ለቦርዱ ያቀርባል፤

2.3.4 የልማት የድርጅቱን መረጃ ለባለ ድርሻ አካላት ይፋ የሚደረግበትን ዘዴ ለይቶ ለቦርድ አቅርቦ ያስወስናል፣ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፤

2.3.5 የሥራ አመራር ቦርድ በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት የልማት ድርጅቱን ወቅታዊ እና ትክክለኛ መረጃ ለባለድርሻ አካላት እና ለተጠቃሚዎች ይፋ ያደርጋል፣ የአፈፃፀም ሪፖርት ለቦርድ ያቀርባል፤

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Public Enterprises Holding and Administration Agency

2.3.6 የልማት ድርጅቱ መረጃዎች ለባለድርሻ አካላት ተደራሽ የሚደረጉበት ዘዴ ይለያል፣ የልማት ድርጅቱ መረጃዎች በየበጀት ዓመቱ ቢያንስ አንድ ጊዜ በዓመታዊ መጽሄት ታትመው እንዲወጡ ይደረጋል፤

2.3.7 በየወቅቱ ለባለድርሻ አካላት ይፋ የሚደረጉ መረጃዎች በሚመለከተው የሥራ ክፍል በአግባቡ ተደራጅተው መቀመጣቸውና መጠበቃቸውን ያረጋግጣል፤

2.3.8 ለባለድርሻ አካላት ይፋ የሚደረጉ መረጃዎች ትክክለኛነት ያረጋግጣል፣ ለባለድርሻ አካላት ይፋ /Disclose/ የሚደረጉ መረጃዎች ትክክለኛ ካልሆኑ ማኔጅመንቱ ተጠያቂ ይሆናል።

ክፍል- ሦስት

3. የዲስክሎዠር ሥርዓት አፈፃፀም መርሆች /principles /

3.1 ግልጽነትና ተጠያቂነት(Transparency and Accountability)፡-

3.1.1 በልማት ድርጅቱ ይፋ የሚደረጉ መረጃዎች በእውነት ላይ የተመሰረቱ፣ የተጠያቂነት መርህ የተከተሉ እና ተአማኒ መሆን አለባቸው።

3.1.2 የልማት ድርጅቱን ገጽታ እና ሁኔታ የሚገልፁ፣ ያጋጠሙ አበይት ክስተቶችና ኩነቶችን የሚያሳይ፣ ትርጉም ያላቸውን (Materially Important) መረጃዎች ማሳወቅ ላይ ትኩረት ማድረግ አለበት፤

3.1.3 ሊሰጡ የሚገባቸውን መረጃዎች መርጦ በመደበቅ ወይም በተድበሠበሠ ሁኔታ ዲስክሎዝ ማድረግ ተጠያቂነትን ያስከትላል፤

3.1.4 ዲስክሎዝ የሚያደርግ አካል በግልጽ መሠየም እና መታወቅ አለበት፤

3.2 **ከህግና አሰራር ጋር የማይቃረን አሰራር(Compliance with Relevant Laws, Regulations and Rules) ስለመዘርጋት:-**

3.2.1 ከልማት ድርጅቱ ይፋ የሚደረጉ መረጃዎች ከአለም አቀፍ፣ ከሀገሪቱ እና ከድርጅቱ ህግና አሰራር በማይጋጭ መልኩ መሆን ይኖርባቸዋል፣

3.2.2 የመንግስት የልማት ድርጅቱ ለባለድርሻ አካላት ይፋ የሚያደርገው መረጃ ትክክለኛነት በሚመለከታቸው አካላት የተረጋገጠ መሆን አለበት፤

3.2.3 የልማት ድርጅቱ ዓመታዊ የፋይናንስ ነክ መረጃዎች ለባለድርሻ አካላት ይፋ የሚሆነው በውጭ ኦዲት ከተደረገ በኋላ መሆን አለበት፤

3.3 **ወቅታዊነት (Timely)**

3.3.1 ለባለ ድርሻ አካላት ይፋ የሚደረጉ የልማት ድርጅቱ የአፈጻጸም መግለጫዎች በየግማሽ ዓመቱ ወቅቱን በጠበቀ መልኩ መሠጠት ይኖርባቸዋል::

3.3.2 የልማት ድርጅቱ የፋይናንስ እና የፋይናንስ ነክ ያልሆኑ መረጃዎች ለባለድርሻ አካላት ይፋ የሚደረጉት ሳይቆራረጥ በእቅድ እየተመራ መሆን አለበት፤

3.3.3 በልማት ድርጅቱ ይፋ የተደረገው መረጃ ለባለ ድርሻ አካላት በበቂ ደረጃ በወቅቱ ተደራሽ ስለመሆኑ በልማት ድርጅቱ የበላይ አመራር መረጋገጥ ይኖርበታል፤

3.4 **ለመረዳት በማያሻማ መንገድ ማቅረብ (Readily Understandable) :-**

3.4.1 በልማት ድርጅቱ ይፋ የሚደረጉ መረጃዎችን እንደአግባቡ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ወይም በሁለቱም ቋንቋዎች ለባለድርሻ አካላት ተደራሽ ማድረግ ይገባል፤ከዚህም በተጨማሪ ተደራሽ ማድረጉ ጠቃሚና አስፈላጊ እስከሆነ ድረስ ሌሎች ቋንቋዎችን መጠቀም ይቻላል፤

3.4.2 በልማት ድርጅቱ ይፋ የሚደረግ መረጃ አሻሚ ባልሆነ እና ሁሉም ሊረዳው በሚችልበት ቋንቋና መንገድ መዘጋጀት አለበት፤

3.5 ፍትሀዊነት (Fairness):-

3.5.1 በልማት ድርጅቱ ይፋ የሚደረግ መረጃ ባለማዳላት ለሁሉም ባለድርሻ አካላት ተደራሽ መሆን አለበት፤

3.6 ቀጣይነት ያለውና የማይቆራረጥ (Consistent) ማድረግ:-

3.6.1 መረጃዎች ወቅታዊ ሆነው ቀጣይነት ባለው መልኩ ሳይቆራረጡ ለባለድርሻ አካላት ዲስክሎዝ መደረግ ይገባቸዋል፤

3.7 ሚስጥር ጠባቂነት(Confidentiality)

3.7.1 እንደየ ልማት ድርጅቱ ባህርይ በሚስጢር መያዝ የሚገባቸው እና በግልጽ ይፋ የሚደረጉት መረጃዎች በቅድሚያ ተለይተው በአሰራር መቀመጥ/ መታወቅ አለባቸው፤

3.7.2 ድርጅቱን ወይም አገርን የሚጎዳ በሚስጢር የተያዘ መረጃ መውጣቱ ከተረጋገጠ ለሥራ አመራር ቦርድ በማሳወቅ ማስተካከያዎች በፍጥነት መደረግ አለበት፣

3.8 ስህተቶችን በአፋጣኝ ማስተካከል ፣

3.8.1 ዲስክሎዝ በተደረጉ መረጃዎች የተሳሳተ መረጃ መኖሩ በታወቀበት ወቅት መረጃው በተለቀቀበት ሁኔታ በአፋጣኝ ማስተካካያ መደረግ ይኖርበታል፤

4. በዲስክሎዠር ሊካተቱ የሚገባቸው አበይት ነጥቦች፣

የልማት ድርጅቶች አፈፃፀማቸውን ለባለድርሻ አካላት እና ለተጠቃሚዎች ይፋ በሚያደርጉበት ወቅት ሊያካትቷቸው የሚገቡ ጉዳዮች የድርጅቱ መግለጫ(Business over view)፣የሰው ሀብት አመራር ሁኔታ(Human Resource management)፣ የማህበራዊ ኃላፊነት፣ የካፒታል ይዞታ (Capital Structure)፣ የኢንቨስትመንት ሁኔታ(Important Current And Future investment)፣ ኮርፖሬት አስተዳደር (Corporate Governance)፣ የፋይናንስ አፈጻጸም (Financial Reports)የአካባቢ ጥበቃ ፣ የህግ ነክ ጉዳዮች፣ የኦዲት ነክ ጉዳዮች ያካትታሉ፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ The Federal Democratic Republic of Ethiopia Public Enterprises Holding and Administration Agency

4.1. የፋይናንስ ነክ መረጃዎች፡-

4.1.1 የካፒታል ምንጭ፣ የካፒታል መጠን፣ የካፒታል መጨመርና መቀነስ በበጀት ዓመቱ ሥራ ላይ የዋለ የኢንቨስትመንትና ሥራ ማስኬጃ በጀት፤

4.1.2 የተወሰደ የሀገር ውስጥና የውጪ ሀገር ብድርና የብድር ክፍያ ያለበት ሁኔታ፤

4.1.3 የድርጅቱ የተጠቃለለ የሂሳብ መግለጫ ወይም ሪፖርት /Consolidated Financial reports/፤

4.1.3.1 የተጠቃለለ የሀብት እና ዕዳ መግለጫ /Consolidated Balance sheet/፤

2.1.3.2 የተጠቃለለ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ /Consolidated Income statement፤

2.1.3.3 የተጠቃለለ የጥሬ ገንዘብ ፍሰት /Consolidated cash Flow statement/መግለጫ፤

4.1.4 ዋና ዋና የፋይናንስ አፈጻጸም ትንተናዎች (Ratio Analysis)፤

4.1.5 በድርጅቱ ትርፍና ኪሳራ ዙሪያ ያሉ ለውጦችና ምክንያቶቻቸው፤

4.1.6 በበጀት ዓመቱ የተከናወኑ ዋና ዋና የፕሮጀክቶች አፈጻጸም እና ቀጣይ የትኩረት ጉዳዮች፤

4.1.7 በውጭ ኦዲት የተሰጡ ዋና ዋና አስተያየቶች፣ የውስጥ ኦዲት ግኝቶችና የተስተካከሉ ወይም እየተወሰዱ የሚገኙ የማስተካከያ እርምጃዎች፤

4.1.8 የግብር እና ታክስ ግዴታ አፈጻጸም መረጃዎች፤

4.2. የፋይናንስ ነክ ያልሆኑ መረጃዎች፡-

4.1.1 የድርጅቱ ዋና መ/ቤትና ቅርንጫፎች አድራሻ/ ደረ-ገጽ፣ ኢ-ሜይል አድራሻ፣ፋክስ ቁጥር፣ ስልክ ቁጥር፤

4.1.2 የድርጅቱ ራዕይ፣ ተልዕኮ ፣ እሴት፣ዓላማ፣ ግቦች እና ስትራቴጂዎች፤

4.1.3 የድርጅቱ የኢንዳስትሪ ባህሪምርትና አገልግሎቶች፤

4.1.4 የድርጅቱ የአስተዳደር አወቃቀር (Governance Structure)፤

4.1.5 የቦርድና የማኔጅመንት አባላት ሙሉ ስም፣ ያላቸው የትምህርት ደረጃ እና ኃላፊነት፤

4.1.6 የድርጅቱ የማኔጅመንት አባላትን እና የሥራ አመራር ቦርድ አባላት ጥቅማጥቅምና ዓመታዊ ክፍያዎች፣ የውስጥ ቁጥጥር ሁኔታና ውጤታማነት፣ የቅሬታ አፈታት ሁኔታና ውጤታማነት፣የስራ አመራር ቦርድ የንኡሳን ኮሚቴዎች አደረጃጀት፤

4.1.7 በበጀት ዓመቱ ለሥራ አመራር ቦርድ፣ለማኔጅመንቱና ለሰራተኞች የተሰጣቸው ጥቅማጥቅምና ማበረታቻ ክፍያ መረጃዎች፤

4.1.8 የልማት ድርጅቱየገበያ ድርሻ መረጃዎች፤

4.1.9 በበጀት ዓመቱ ታቅደው የተከናወኑ የኦፕሬሽን ስራዎች በዋና ዋና አመለካቾች ፤

4.1.10 የተገልጋይ እርካታ ያለበት ደረጃ፤

4.1.11 የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነትን ከመወጣት አኳያ የተከናወኑ ተግባራት፣ የተገኙ ውጤቶችና የማህበረሰብ/ አካባቢ አጠባበቅ፤

4.1.12 ዋና ዋና የስጋትምንጮች፣ የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች እና የተገኙ ውጤቶች፤

4.1.13 በቁልፍ ቦታዎች የተኪ የሰው ሃይል የማፍራት ዕቅድ አፈጻጸም ደረጃ፤

4.1.14 ከድርጅቱ መደበኛ ሥራዎች ጋር የተያያዙ ህግ ነክ ጉዳዮችና እንድምታቸው፤

4.1.15 ድርጅቱ ያገኛቸው የተለያዩ የጥራት ማረጋገጫ ሰርተፍኬቶችና ዕውቅናዎች፤

5 የመረጃዎችን ሚስጢራዊነት በተመለከተ፤

5.1 በልማት ድርጅቱ በሚስጢር መያዝ ያለባቸው መረጃዎች በመለየት የመረጃ ሚስጢራዊነት ለመጠበቅ ፖሊሲ በድርጅቱ ተዘጋጅቶ በስራ አመራር ቦርድ በማጸደቅ ተግባራዊ መሆን አለበት፡፡

5.2 ከላይ በንኡስ አንቀጽ 5.1 የተጠቀሰው እንዳለ ሆኖ ይፋ የማይደረጉ መረጃዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ጉዳዮችን ያልተካተቱ መሆናቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት መሆን ይኖርበታል፡፡

5.2.1 የሀገር ደህንነት እና የማህበረሰብ ስብዕናን የሚጎዱ መረጃዎች፤

5.2.2 የድርጅቱ ህልውና እና ተወዳዳሪነትን አደጋ ላይ የሚጥሉ መረጃዎች፤

5.2.3 የድርጅቱን መልካም ዝና የሚጎዱ መረጃዎች፤

5.2.4 ድርጅቱ ከሌሎች አካላት ጋር በሚስጢር ለመጠበቅ ግዴታ የገባባቸው ጉዳዮች፤

5.2.5 በሌሎች የልማት ድርጅቶች እና ተቋማት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ መረጃዎች፤

6 የዲስክሎዠር አፈፃፀም ሥርዓት ዘዴዎች፣

6.1 የልማት ድርጅቱ በተለያዩ መንገዶች የድርጅቱን የፋይናንስና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ መረጃዎች በድረ-ገጽ፣ በመጽሄት፣በጋዜጣ፣ በብሮሸር፣ በቴሌቭዥን፣ በሬድዮ እና ሌሎች ተደራሽ በሆኑ የብዙሃን መገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ይፋ ማድረግ ይችላል፤

6.2 ለኤጀንሲው ተጠሪ የሆኑ የልማት ድርጅቶች ዓመታዊ የተጠቃለለ ዲስክሎዠር(Aggregate Disclosure) በኮርፖሬት ኮሚኒኬሽን ወይም በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት ተዘጋጅቶ ለባለድርሻ አካላት ይፋ መደረግ ይኖርበታል፤

6.3 ዲስክሎዠ በተደረጉ መረጃዎች ከባለድርሻ አካላት ግብረ- መልስ ለመቀበል የሚያስችል ዘዴ መፈጠር ይኖርበታል፡፡

7 የዲስክሎዠር አፈጻጸም የጊዜ ሰሌዳ

7.1 በግማሽ ዓመት ይፋ የሚደረጉ መረጃዎች፤

7.1.1 በድረገጽ፣ በጋዜጣ፣ በብሮሼር፣ በቴሌቭዥን፣ በሬድዮ እና በሌሎች ተደራሽ የሆኑ የብዙሃን መገናኛ ዘዴዎች በመጠቀም በበላይ አመራሩ ዕውቅና ይፋ የሚደረግ ሆኖ የግማሽ ዓመቱ የፋይናንስና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ መረጃዎች አፈጻጸም ባካተተ መልኩ ይፋ መሆን አለበት፡፡

7.1.2 የግማሽ ዓመቱ የድርጅቱ መረጃዎች ይፋ የሚሆነው የግማሽ ዓመቱ በተጠናቀቀ አንድ ወር ውስጥ መሆን አለበት፤

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Public Enterprises Holding and Administration Agency

7.2 በየዓመቱ ይፋ የሚደረጉ መረጃዎች፤

7.2.1 በድረ-ገጽ፣በመጽሄት፣በጋዜጣ፣በብሮሹር፣በቴሌቭዥን፣በሬድዮ እና በሌሎች ተደራሽ የሆኑ የብዙሃን መገናኛ ዘዴዎች በመጠቀም በበላይ አመራሩ ዕውቅና ይፋ የሚደረግ ሆኖ ዓመታዊ በውጭ ኦደተር የተረጋገጠ የፋይናንስ እና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ መረጃዎችን አፈጻጸም ባካተተ መልኩ ይፋ መሆን አለበት፡፡

7.2.2 የልማት ድርጅቱ ዓመታዊ መረጃዎች ይፋ የሚሆነው የውጭ ኦዲት ሪፖርት ቀርቦ በተገመገመ አንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይሆናል፡፡

8 ተፈጻሚነት የሌላቸው መመሪያዎች እና አሰራሮች፡-

ከዚህ በፊት የወጣው የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የዲስክሎዥር አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር ኮር/002/2011 እና ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያና የአሰራር ልምድ በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

9 ስለመመሪያው መሻሻል፡-

ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በኤጀንሲው ሊሻሻል ይችላል፡፡

10 መመሪያው በሥራ ላይ የሚውልበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከጥር 2011 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

በየነ ገ/መስቀል

የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ